# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 285 ጥቅምት 15 2006 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

በግንቦት 7 እምነት ትግሉ በሁሉም ሥፍራ ነው። ኢትዮጵያዊያን በያለሉበት ቦታ በተደራጀና በተቀናጀ መልክ ወያኔን ፊት ለፊት ከተጋፈጥን የድላችን ቀን እናቀርባለን።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## የግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ጠንካራ የሕዝብ ደጀን እንዳለው አስታወቀ እስከመጨረሻው አብረን እንቁም ሲልም ጥሪውን አሰማ

በኖርዌ የተደረገውን የግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ግሩም ድንቅ የገቢ ማሰባሰቢያ ጨምሮ ከሌላውም የዓለም ክፍል ከፍተኛ ድጋፍ እየተደረገለት መሆኑን ሕዝባዊ ሃይሉ ገለጸ። ይህንን ተከትሎም የአብረን እንታገል ጥሪ ከያቅጣጫው እየጎረፈለት መሆኑንም ጠቁሟል። ፋሽስት ወያኔ አንዴ በሲማሊሞ አቋርጡ ሌላ ጊዜ ደግሞ መንገዱን ጨርቅ የርግላችሁ ሲል እንደነበር ያስታወሰው ሕዝባዊ ሃይሉ ይኸው ያ ቀን ደርሷል ብሏል።

ባገዛዙ መሪዎች የውስጥ ሽኩቻ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው አባላት መልቀቅና በሰራዊቱ ውስጥ እየሰፋ የመጣው አለመረጋጋትና ለማን ነው የምንሞተው ጥያቄ ፋሽስት ወያኔን ሰላም እንደነሱት የታወቀ ሲሆን በሀገር ውስጥ እያየለ የመጣው መገዛት መረረን፣ ጥያቄያችን ይደመጥ፣ ነጻነት አጣንና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ለወያኔ ለመፍታት ያስቸገሩ እንደሆኑበት ታውቃል።

ከድጡ ወደ ማጡ እነዲሉ የግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ድንገት ብቅ ማለትና አስፈሪነቱ በፍጥነት መጨመሩ የወያኔ ዜና ማሰራጫዎችን አቅጣጫ ሙሉ በሙሉ ቀይሮት እንደነበር ሲታወስ ከህዝባዊ ሃይሉ እየተባሉ ያሉት ሁሉ እውነት እንደሆኑ የሚያረጋግጡ ናቸው የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም።

ወደ ሕዝባዊ ሃይሉ እየተቀላቀለ ያለው ኢትዮጵያዊ ቁጥር ከግምት በላይ ቢሆንም ያለ የሌለ አቅሙን ተጠቅሞ ወታደራዊ ስልተናውን ከመቼውም ጊዜ በሰፋ መልኩ በመስጠት ላይ እንደሆነ ሕዝባዊ ሃይሉ ጠቁሟል። "እኛ ለሂዎታችን ሳንሳሳ ለሀገራችን ለመሞት በትክክለኛው ቦታ ላይ እንገኛለን እናንተ ደግሞ በደጀንነታችሁ ጠንክሩ፤ ሁለቱም ትግል ነው" ያለው ሕዝባዊ ሃይሉ፣ ከዚህ በፊት የተደረጉለትን እገዛዎች አድንቆ ምስጋናውን በማቅረብ የፋሽስት ወያኔ ግብአተ መሬት እስኪተገበር አብረን እንቁም ሲል ጥሪውን አቅርቧል።

## ፋሽስት ወያኔ አሁንም በማስፈራራት ዘመቻው እየገፋበት መሆኑ ተጠቆመ

የጎጠኛው መለስ ሙት መንፈስ ሃይለማሪያም ደሳለኝ አሁንም በማስፈራራቱ ገፍቶ ስለሙብቱ የጠየቀም ሆነ ለመጠየቅ የተሰናዳ በሙሉ አሸባሪ ነው በማለት ጠቅሶ አሸባሪዎችን ደግሞ እንቀጣቸዋለን ብሏል። የተቃዋሚዎች ትግል ለራሱም ጭምር ነጻ መውጣት ጠቃሚ መሆኑን የዘነጋው ሃይለማሪያም "የተቃዋሚዎችን እንቅስቃሴ እየተከታተልን ነው በቅርቡ እናሳያችኋለን" ሲልም አላዝኗል። በገደምዳሜም እነሱን ለማሰር የሚያስችለንን የውሸት መረጃ እያጠናከርን ነው፤ አኬልዳማ ወይም ጅሃዳዊ ሃረካት ቀጣዩ ክፍል ሰርተን ስናጠናቅቅ ሁሉንም ሰብስበን ዘብጥያ በማውረድ እናሳያችኋለን አይነት ንግግር እድርጋል። ፈራችሁ እያላችሁም ህልማችሁን አትንገሩን እኛ ፈጽሞ አንፈራም ሲልም አክሏል።

ሕዝብን በማስፈራራት እንዲመርጡት በማስገደድና የምርጫ ኮሮጆ በመስረቅ 99.6 በመቶ ተመረጥኩ እያለ የሚለፈውን ፋሽስት ወያኔ አሳምረው የሚያውቁ ወገኖች ግን "ፋሽስት ወያኔ ድብን አርጎ ይፈራል" ብለዋል። አክለውም "ሕዝቡን በዘርና በሃይማኖት በመከፋፈል፣ ወጣቱን ስራ በማሳጣት ሀገር ጥሎ እንዲሰደድ በማድረግ፣ የትምህርትን ጥራት በመግደል ምንም መፍጠር የማይችል ዜጋ በማፍራት፣ የኢትዮጵያን ታሪክ በማጥፋትና ሉአላዊነቷን በማስደፈር የሰራው ወንጀል ሳይበቃው የኑሮ ውድነትን ጣራ እንዲነካ በማድረግ ሁሉንም ዜጋ የወያኔ ተለጣፊ ለማድረግ የሚያደርገው ጥረት በሕዝብ እንዲተፋ ያደረገው መሆኑ የሚታወስ ሲሆን የህዝባችንን የመናገር፣ የመጻፍና የመንቀሳቀስ ነጻነት በመንፈግ ሀገሪቱን ወደ ትልቅ እስር ቤትነት እየቀየራት ያለው ፋሽስት ወያኔ ባይፈራ ነበር የሚደንቀው" ብለዋል።

የወያኔው ሕገመንግስት በሚፈቅደው መሰረት የተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ የጎዳና ላይ ነውጥ ከተባለ፤ ከወያኔ በቀር ሌላ የተሸበረ ሳይኖር ንጹሃን ዜጎችን በተቀነባበረ መንገድ ያለምንም ማስረጃ አሸባሪ እያሉ ዘብጥያ ማውረድ ምን ሊባል ነው" የሚሉ ሌሎች ወገኖች ደግሞ "የወያኔ ፍርሃት አንድና ሁለት የለውም፤ ከዚህ የልቅ 'የፈሪ በትር ሆድ ይቀትር' እንደሚባለው ከዚህ ፍርሃት በኋላ ሊወስድ የሚችለው በሀሰት ላይ የተመሰረተ እርምጃ ጥልቀት ነው የሚያሳስበው" ካሉ በኋላ "የሰሞኑ የወያኔ ሰራዊት ከቀድሞው የተለየ እንቅስቃሴ፣ ስለ ግንቦት 7 ሕዝባዊ ሃይል ከይስሙላው ፓርላማ እስከ ሁሉም የወያኔ የዜና ማሰራጫዎች ከጠዋት እስከ ማታ የሚደረገው ውግዘትና ለፈፋ፣ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ኦብነግ በወያኔን ባለስልጣናት ጥቃት መፈጸሙን አሳወቀ

ኦብነግ በሚል ምህጻረ ቃል የሚታወቀዉ የኦጋዴን ነጻነት ግንባር በም/ጠ ሚኒስትርና የትምህርት ሚኒስቴር ደመቀ መኮንን በሚመራው የወያኔ ልኡካን ቡድን ላይ ጥቃት ፈጽሞ በርካታ ወታደሮችን መግደሉን ግንባሩ ቃል ለኢሳት በሰጠዉ ጋዜጣዊ መግለጫ ገለጸ። የግንባሩ ቃል አቀባይ የሆኑት አቶ ሀሰን አብዱላሂ ለኢሳት ቴሌቪንና ሬድዮ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታዉቁት ኦብነግ ይህንን ወያኔን ያስደነገጠዉን ጥቃት የፈጸመዉ ደመቀ መኮንንና ቁጥራቸዉ ወደ ዘጠኝ የሚጠጋ የክልሉ መሪዎችና ባለኃብቶች በአንዳንድ የኦጋዴን አካባቢዎችን ጉብኝት ለማድረግ ቀብሪደሀር አየር ማረፊያ ባረፉበት ወቅት ነው። እንደ አቶ ሀሰን አብዱላሂ አገላለጽ ኦብነግ የእነደመቀ መኮንንን ጉብኝት በተመለከተ መቼ እንደሚመጡ፤ እነማን እንደሚመጡና ዬት ዬት በታዎችን እንደሚጎበኙ አስቀድሞ ሙሉ መረጃ አግኝቶ ስለነበር ጥቃቱን ለመፈጸምና አጥቂ ቡድኑ ጉዳት ሳይደርስበት በፍጥነት ለመሰወር እንዲችል በቂ ዝግጅት መደረጉን ተናግረዋል። በወያኔው ተላላኪ አሸከር እና የኢትዮጵያን ለም መሬት ለሱዳን አሳልፎ በመስጠት በፊርማው ያረጋገጠው ባንዳው ምክትል ሚኒስቴር ተብዬ ደመቀ መኮንን በሚመራው የልኡካን ቡድን ላይ የኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር ታጣቂዎች በፈጸሙት ጥቃት በርካታ ወታደሮች እንደተገደሉ ግንባሩ አስታውቋል። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አልጠግብ ባዩ ወያኔ አሁንም የጎንደርን ግዛት ቆርሶ ከትግራይ ጋር ለመቀላቀል እየታገለ ነዉ

በ1983 ዓም አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ወልቃይት ጠገዴንና አካባቢዉን ከጎንደር ቆርሶ ከትግራይ ጋር የቀላቀለዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ አሁንም እንደገና ፊቱን ወደ ጎንደር በማዞር አጎራባች የጎንደር ወረዳዎችን ቆርሶ የትግራይ ክልል አካል ለማድረግ እየተሯሯጠ መሆኑን የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ልሳን የሆነው ፍኖተ-ነፃነት በቅርቡ ባወጣዉ እትሙ ዘገበ። "አባይ ትግራይ" ወይም ታላቋ ትግራይ ብሎ የበረሃ ትግል የመጀመረዉና ዛሬ ኢትዮጵያን የሚቆጣጠረዉ ወያኔ በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር ዞን ስር የሚገኙትን አብረሃ ጅራ እና አብደራፊ የተባሉ ሁለት ወረዳዎች ከትግራይ ክልል ጋር ለመቀላቀል የሚያደርገዉን ጥረት በመቀጠል በሁለቱ ወረዳዎች ዉስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸዉን የትግራይ ገበሬዎች በማስፈር ላይ መሆኑ ታዉቋል። አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙና ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ ምዕራባዉያንና የአገር ዉስጥ የፖለቲካ ተንታኞች ይህንን ወያኔ የጀመረዉን የራሱን ገበሬዎች የማስፈር ዘመቻ "አስተዳደራዊ የግዛት ቅሚያ" ብለዉታል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የ40/60 መኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች ቤቱን እራሳችሁ ስሩ ተባሉ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን የቤት እጦት ለማቃለል መንግስት የ40 በ 60 መኖሪያ ቤት ሠርቶ ለማስረከብ ዝግጁ ነዉ ብሎ የሰጠውን መግለጫ አምነው መክፈል የሚገባቸዉን ሙሉ ክፍያ የከፈሉ ከ81 ሺህ በላይ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ወያኔ የገባላቸዉን ቃል ቀይሮ ቤቱን እራሳችሁ ስሩ ብሏቸዉ ችግር ላይ መዉደቃቸዉን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዜና ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። ቤት ፈላጊዎቹ መንግስት በገባላቸዉ ቃል መሰረት የእነሱ ድርሻ የሆነዉን 40% ለመንግስት ገቢ ካደረጉ በኋላ መንግስት በገባዉ ቃል መሰረት ቤቱን ሰርቶ ማስረከብ ሲገባዉ ሀሳቡን ቀይሮ ከፋዮቹ በማህበር ተደራጅተው ቤቱን እራሳቸው እንዲሠሩ መወሰኑ የቤተሰቦቻቸዉንና የእራሳዉን ፍላጎት ጎድተዉ ገንዘብ የቆጠቡትን ዜጎች መወጣት የማየችሉት ችግር ዉስጥ ከትቷል። እንዲህ አይነቱ የወያኔ አሰራር የተለመደና ወያኔ እሱ የሚፈልገዉ ነገር ከተሟላለት ምንም ነገር ተናግሮ በቃሉ የማይጸና ከሀዲ መሆኑን ብዙዎች በተለያየ ግዜ በማስረጃ አሳይተዋል። ለምሳሌ ብዙ የዳያስፖራ አባላት ኑና "ቤት ግዙ" የሚባል ወጥመድ ዉስጥ አይናቸዉ እያየ ሲገቡ አገር ዉስጥና በዉጭ አገሮች የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና እንዲሁም የሞያዉ ብቃት ያላቸዉ ኤክስፐርቶች የቤት ግዢዉ ኢንቨስትመንት የማያዋጣና ጭራሽ ላይመለስ የሚችል ኢንቨስትመንት መሆኑን በተደጋጋሚ መናገራቸዉ ያታወሳል። ይህ በቅርቡ ወያኔ አገር ቤት አጠገቡ ላሉት ኢትዮጵያዉያን ያሳየዉን ክህደት ቅርብ ሆነዉ ሊካራከሩት በማይችሉት የዳያስፖራዉ አባላት ላይ የማያሳይበት ምንም ምክንያት የለም።

እንደ ዘገቢዎቻችን አባባል ከሆነ በአሁኑ ጊዜ መቶ በመቶ የከፈሉ የ40/60 ተመዝጋቢዎች በመኖርያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ወደ ተነደፈው ፕሮግራም እንዲዛወሩ የአዲስ አበባ አስተዳደር እያግባባቸዉ መሆኑ ታዉቋል። ሆኖም ክፍያ የፈፀሙ ዜጎች በመኖርያ ቤት ኅብረት ሥራ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ሕዝባዊ እምቢተኝነት በውጭ አገር፤ እንዴት?

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሁለገብ ትግል ወያኔ ማስወገድ ይገባል ብሎ የሚያምና ለዚህም የሚታገል ድርጅት ነው። "ሁለገብ ትግል" ሲባል ሰላማዊም ሰላማዊ ያልሆኑም የትግል ስልቶችን መጠቀም ማለት ነው። "ሁለገብ ትግል" ሲባል በአገር ውስጥም ከአገር ውጭም የሚደረጉ ትግሎች ማለት ነው።

ከዚህ አንፃር በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሚና ምን ሊሆን ይገባል?

በግንቦት 7 እምነት በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በድጋፍ ሰጭነት ሳይወሰኑ የትግሉ ቀጥተኛ ተሳታፊዎች መሆን ይኖርባቸዋል። በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በወያኔ ጥቅሞችና ተቋማት ላይ በማመጽ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያን አርዓያ መሆን ይኖርባቸዋል።

በዚህ ረገድ የተጀመሩ አበረታች ጥረቶች አሉ፤ ለምሳሌ:

1. ወያኔ ሙስሊሞችን ከክርስቲያኖች ለማጣላት ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም። በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን "እንቢ አንጣላልህም" ያሉት መሆኑ የሚያኮራ ነው። ወያኔ ከጠበቀው በተቃራኒ የሁለቱም ሃይማኖቶች መሪዎች በጋራ ጉዳዮች ላይ ሲመክሩ መታየቱ ተስፋ ሰጪ ጅማሮ ነው። አብሮነታችንን ማጎልበትና ይህንን በአደባባይ፣ በአዳራሾች፣ በቴሌቪዥን መስኮቶች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማሳየት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። ውጭ የተጀመረው አገር ቤት መዳረሱ የማይቀር ነው። ይህ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርብናል።
2. ወያኔ በአባይ ግድብ ስም በውጭ አገራት ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በርከት ያለ ገንዘብ እንደሚያገኝ ተስፋ አድርጎ የነበረ ቢሆንም ኢትዮጵያዊያን "ከአባይ በፊት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ይገደብ" "ከአባይ በፊት ሙስና ይገደብ" እያሉ ወዋጮዎቹን እንቢ ብለዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ እስካሁን የታየው ጽናት በጣም አበረታች ነው። የወያኔ ሹማምንት በአባይ ጉዳይ እንኳንስ ገንዘብ ስብሰባም ሊሰበሰቡ አልቻሉም። ይህም ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።
3. ኢትዮጵያዊያን በስፖርትና በኪነጥበባት መስኮች የሚያደርጓቸው መሰባሰቦች ለትግሉ ትልቅ እገዛ ይሰጣሉ። የኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን በሰሜን አሜሪካ (ESFNA) ከወያኔና ከወያኔ ሸሪክ ቱጃር ጋር ያደረገው ትንንቅ የሚያኮራ ነው። በርካታ ኢትዮጵያዊያን አገር፣ ነፃነት፣ ክብር ይበልጥብኛል ብለው የቀረቡላቸውን አጓጊ ማባበያዎችን "እንቢ" ብለዋል። ይህ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።
4. ባለፈው ዓመት ጋዜጠኛ አበበ ገላው በመለስ ዜናዊ ላይ፤ ዘንድሮ ደግሞ ጋዜጠኛ ሳዲቅ አህመድና አቶ መስፍን የዘረኛው ወያኔ ግንባር ቀደም አስተባባሪ በሆነው ስብሀት ነጋ ላይ ያሰሙት ተቃውሞ በጣም የሚደገፍ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ተቃዉሞ በውጭ አገራት የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ባህል ሊሆን ይገባዋል።
5. በስዊድን የሚገኙ የሕግ ባለሙያዎች የጀመሩት እና በኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ ተሳትፎ እየተካሄደ ያለው የወያኔ ወንጀለኞችን ወደ ፍርድ የማቅረብ ሂደት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

እነዚህ መልካም ሥራዎች ምሳሌቶች ሲሆኑ በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ከዚህ በላይ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። አንዳንዱን ለአብነት ያህል ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1. በአገራችን ውስጥ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ እንዲመጣ ከፈለግን ወያኔን ማስደንገጥ፣ ማሸበር፣ ካስፈለገም ማስወገድ የሚችል የአመጽ ኃይል መኖሩ ወሳኝ ነው። እንዲህ ዓይነት የወገን ኃይል ከጀርባው መኖሩ ሲሰማው ነው ሕዝብ ለእንቢተኝነት የሚነሳሳው። በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ይህንን ኃይል ቢቻል መቀላቀል፤ ካልተቻለም በአባላት ምልመላ፣ በፋይናንስ፣ በሎጂስቲክስና ዲፕሎማሲ መደገፍ ይጠበቅባቸዋል። ይህ ከሁሉ የላቀ የእምቢተኝነት መገለጫ ነው።
2. ትግሉ እየመረረ መሆኑ በመረዳት በርቀት ሆነን ከመብሰክሰክ በትግል ላይ ያሉትን ድርጅቶች መቀላቀል ሌላው አሁኑኑ ልናደርገው የሚገባ ነገር ነው። ድርጅቶች "አይረቡም" ብለን ስላጣጣልናቸው አይጠናከሩም። ድርጅቶችን ማጠናከርና ማዘመን ያለብን እኛው ነው። መሪዎችን ማውጣት ያለብን እኛው ነው። እስካሁን ድርጅቶችን ያልተቀላቀልን ካለን መቀላቀልና ትግሉን ማጧጧፍ ይኖርብናል።
3. በየተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ወያኔን "እንቢ" እንበል። "እንቢ" የማለትን አጋጣሚ ማሳለፍ የለብን። "እንቢ" ማለት የምንችልባቸው አጋጣሚዎች ብዙዎች ናቸው። ለምሳሌ: -

ሀ) ወያኔ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታን አዲስ የገንዘብ ማለቢያ ለማድረግ አቅዶ ተነስቷል። ወደ ሚሊዮን የሚጠጉ ቤቶችን በ2 ዓመት ጨርሼ አስረክባለሁ በሚል ማባበያ በውጭ አገራት ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ገንዘብ ለመሰብሰብ ዝግጅቱን አጠናቋል። ይኸንን ነገር አጠንክረን "እንቢ" ማለት ይኖርብናል። "ለኛ ቤት ከመሰጠቱ በፊት፤ የተፈናቀሉ ወገኖቻችን መወደቂያ ያግኙ" ማለት ካልቻልን በራሳችን ማፈር አለብን። የአውሮፓና የአሜሪካ መንግሥታትን አምባገነኖችን በገንዘብ አትደግፉ እያልን እኛ ራሳችን ወያኔን በገንዘብ የምንደግፈው ከሆነማ ከነሱ ብሰን መገኘታችንን እንወቀው።

ለ) ወያኔ በስደተኛ ስም በመካከላችን የሰገሰጋቸውን ካድሬዎችን የማጋለጥ ዘመቻ ማፋፋም አለብን። የወያኔ ደጋፊዎችን በኤርትራ ስደተኞች ስም እንደሚገቡ መረጃዎች አሉ። በደል ደርሶብናል ብለው መንግሥታትን አሳምነው የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙ በኋላ አጠቃን ካሉት አገዛዝ ጋር የሚሠሩ መሆናቸው የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን አጠናቅረን ለየሀገሩ መንግሥታ ማቅረብ እንደ አቢይ ሥራ መያዝ ይኖርብናል።

ሐ)የወያኔ ባለሥልጣናት የሚገዟቸውን ቤቶች፤ የሚያስተዷድሯቸውን ቢዝነሶች እያደንን ማጋለጥ ይኖርብናል።

መ)የወያኔዎች ሹማምንት በአሜሪካና አውሮፓ በነፃነት ሊዘዋወሩ አይገባም። በሄዱት ሁሉ ተቃውሞና ውርደት ሊከተላቸው ይገባል።

ሠ)የወያኔ ቢዝነሶች ላይ ማዕቀብ ማድረግን (ቦይ ኮት) መልመድ አለብን። ጥረቶቻችንን በፈጠራ ከደገፍን ወደ አገር ቤት የምንልከው ገንዘብ የወያኔ የውጭ ምንዛሬ ረሀብ ማስታገሻ የማይሆንበት መንገድ መሻት አለብን።

ረ) ለወያኔ ባለሥልጣኖች ዲግሪ የሚያድሉ ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆችን ማዋረድ መጀመር አለብን። ስምንተኛ ክፍል እንኳን በወጉ ላልጨረሱ ሰዎች የማስትሬት ዲግሪ እንደሰጡ ማሳወቅ የኛ ኃላፊነት መሆን አለበት።

በግንቦት 7 እምነት ትግሉ በሁሉም ሥፍራ ነው። ኢትዮጵያዊያን በያለሉበት ቦታ በተደራጀና በተቀናጀ መልክ ወያኔን ፊት ለፊት ከተጋፈጥን የድላችን ቀን እናቀርባለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## የ40/60 መኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ማኅበራት ፕሮግራም ተደራጅተው ቤቶችን ሲገነቡ፤ ህጉ ከይዞታቸው ለሚፈናቀሉ ሰዎች ራሳቸው ካሳ እንዲከፍሉ ስለሚያስገድዳቸው አዲሱ የመንግስት ሀሳብ ብዙዎችን ስጋት ላይ ጥሏቸዋል። መንግስት ክፍያ የፈፀሙት በማህበር እንዲደራጁ ለጀመረው ማግባባት እስካሁን ምላሽ ያገኘው ከ አንድ በመቶ ያህሉ ብቻ እንደሆነም ተገልጿል።አንድ የከተማው አስተዳደር ከፍተኛ ባለሥልጣን ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ አስተዳደሩ ከ40/60 ቤቶች ፕሮግራም ውስጥ መቶ በመቶ የከፈሉት ወደ ማኅበራት እንዲዛወሩ የተፈለገው እነዚህ ወገኖች መቶ በመቶ የመክፈል አቅም ካላቸው፣ የራሳቸውን ቤት ራሳቸው እንዲገነቡና መንግሥት ላይ ያለው ጫና እንዲቀንስ በሚል ሐሳብ ነው ብለዋል።

በሦስቱም የመኖርያ ቤቶች ማለትም በ40/60፣ በ10/90 እና በ20/80) ፕሮግራሞች የተመዘገቡ ነዋሪዎች 2.5 ቢሊዮን ብር እንደቆጠቡ፤ ይሁንና የእነዚህን ቤቶች ግንባታ ለማስጀመር መንግሥት ተጨማሪ 7.5 ቢሊዮን ብር እንደመደበ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ባለፈው ሐሙስ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ገልፀው ነበር። ዜጎች የመንግስትን ቃል አምነው ክፍያ ከፈፀሙ በሁዋላ መንግስት ሀሳቡንና አሠራሩን መቀየሩ ከህግ አኳያ ውል እንደማፍረስ ነው ያሉ አንድ የህግ ባለሙያ፤ ሁኔታው ከዚህም ባሻገር ፕሮግራሙ ሲጀመር:- "መንግስትን አምናችሁ እንዴት ገንዘባችሁን ቀድማችሁ ትከፍላላችሁ እያሉ ሲመክሩ የነበሩ ዜጎችን ስጋት ተገቢነት" ያመላከተ ነው"ብለዋል።

## አልጠግብ ባዩ ወያኔ አሁንም የጎንደርን ግዛት ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔን የግዛት ዝርፍያ ለመከላከል የወረዳዉ ነዋሪዎች አንቅስቃሴ መመራቸዉ እየተሰማ ነዉ። የሳንጃ፣ የጠገዴ፣ የዳባትና የአፎኛ ደምቢ ወረዳ ነዋሪዎች ወያኔ የጎንደርን ግዛት የራሱ ለማድረግ የሚያደርጉዉን ጥረት በሙሉ ኃይላቸዉ እንደሚቃሙትና እንቅስቃሴዉ የማይቆም ከሆነ ምንም አይነት እርምጃ ከመዉሰድ እንደማይቆጠቡ አሳዉቀዋል። የአማራን ተወላጆች ዕድሜ ልካቸዉን ከኖሩባቸዉ ቦታዎች "የእናንተ ክልል" አይደለምና ዉጡ እያለ ከጉራፈርዳና በቅርቡ ከቤንሻንጉል ክልል ያፈናቀለዉ ወያኔ የትግራይ ገበሬ የሰፈረበትን ቦታ ሁሉ ወደ ትግራይ ክልል መቀላቀሉ የሚያሳየዉ ነገር ቢኖር ወያኔ ኢትዮጵያ ለምትባል ታሪካዊ አገር ምንም ደንታ እንደሌለዉና ታላቋን ትግራይ እዉን ለማድረግ የሚታገል ፍጹም ዘረኛ መሆኑን ነዉ ሲሉ አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ አደራ ያሉን የክልሉ ባለስልጣን ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በስልክ ባደረጉት ምልልስ ተናገሩ። ባለስልጣኑ ካሁን በኋላ አይናቸዉ እያየ የአማራ ክልል በትግራይ አይዘረፍም ካሉ በኋላ ይህንን ለማድረግ ደግሞ እሳቸዉና ተከታዮቻቸዉ ወያኔን ለማስወገድ የትጥቅ ትግል የጀመሩ ወጎኖችን እንደሚቀላቀሉ ተናግረዋል።

---

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን
የፖስታ ሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

# ወያኔና አላርፍ ያለች ጣት አንድ ናቸዉ

- “ለምንድነዉ የመረጃ ምንጫችን ኢቲቪ ብቻ የሚመስላችሁ - እኛኮ መኃይሞች አይደለንም!”
- “እንደ አፍጋኒስታንና ፓኪስታን ለምን ታዩናላችሁ፤ ለምንስ የእናንተን ብቻ እንድንሰማ ታስገድዱናላችሁ?”
- “ቀይ መስመር ዬት ቦታ እንደሚሰመር ማወቅ አለባችሁ - ቀይ መስመር በሰዉ ልጆች መብት ላይ አይዘረገም!”

ውድ አንባቢዎቻችን እነዚህን የወያኔን ባዶነትና መኃይምነት ቁልጭ አድርገዉ የሚያሳዩ ከፍተኛ መልዕክት የተሸከሙ ኃይለ ቃሎች የተናገሩት የወደፊቷ ኢትዮጵያ ተስፋ የሆኑት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ናቸዉ። መልዕክቱ የተላላፈዉ ደግሞ ባለፈዉ ሳምንት ለአለማያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሽብርተኝነትንና አክራሪነትን በተመለከተ ስልጠና ለመስጠት ለሄዱት ለወያኔ መሪዎችና ካድሬዎች ነዉ። ከተማሪዎቹ ንግግር በግልጽ አንደምንረዳዉ ከአቅማቸዉ ዉጭ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ለማሰልጠን የሄዱት የወያኔ ካድሬዎች እነሱ እራሳቸዉ በኢትዮጵያ ወቅታዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ በቂ ስልጠና ተሰጥቷቸዉ ወደመጡበት ተመልሰዋል። ይህ አለማያ ዩኒቨርሲቲ ዉስጥ ለሰአታት በወያኔ ካድሬዎችና በዩኒቨርሲቲዉ ተማሪዎች መካከል የተካሄደዉ ዉይይት በግልጽ ያሳየዉ አንድ ቁም ነገር ቢኖር ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ምን ያክል ሆድና ጀርባ እንደሆኑ ብቻ ሳይሆን የወያኔ መሪዎች በሄዱበት ቦታ ሁሉ ከፍተኛ ህዝባዊ ተቃዉሞ ገጥሟቸዉ አንገታቸዉን የሚያቀረቅሩት በዉጭ አገሮች ብቻ ሳይሆን በአገር ቤትም መሆኑን ነዉ።

ባለፈዉ ሳምንት አገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ አገር የሚኖረዉ ኢትዮጵያዊ በድረገጾች፤ በሬድዮ፤ በፓልቶክ፤ በየቤቱና በየቡናቤቱ በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ አሰጥ አገባ ሲል ከርሟል። አንዱና የብዙ ኢትዮጵያዉያንን ቀልብ የሳበዉ ጉዳይ የአፍሪካ አገሮች በወያኔ አስተባባሪነት የአለም አቀፉን ፍርድ ቤት የፈጠረዉን ስምምነት ረግጠዉ ለመዉጣት የሚያደርጉት ጥረት ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ ሽብርተኝነትንና አክራሪነትን አስመልክቶ መስጠት የጀመረዉ ስልጠና ጉዳይ ነዉ። በነገራችን ላይ እነዚህን ጉዳዮች ለአቀራረብ እንዲመቸን በሁለት ከፈልናቸዉ አንጂ የተያያዙና የቆሻሻ መጠራቀሚያ ከሆነዉ የወያኔ ጭንቅላት የመነጩ ተመሳሳይ ሀሳቦች ናቸዉ። አላማቸዉና ግባቸዉም ተመሳሳይ ነዉ። ወያኔ በቅርቡ ሥልጠናና ገለጻ እያለ የጀመረዉ ግርግር አላማዉ ለመብቱና ለነጻነቱ አምርሮ መታገል የጀመረዉ የኢትዮጵያ ህዝብ መታገሌ ሽብርተኛ ሊያሰኘኝ ይችላል ብሎ እንዲፈራ ሲሆን ኢትዮጵያን ከአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ለመነጠል የሚደረገዉ ጥረት ደግሞ የወያኔ መሪዎች ለፈጸሙት የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዳይጠየቁ ለማድረግ ነዉ።

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ሠላማዊ ሰልፍ ወጥቶ የተቃወማቸዉን ሽብርተኛ፤ የማምለክ መብቴን አትንኩ ብሎ የጠየቃቸዉን ደግሞ አክራሪ እያሉ የሚያስሩትና የሚደበድቡት በእርግጥም እነዚህ ሰዎች አክራሪዎችና ሽብርተኞች ሆነዉ አይደለም። ይህንን ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ወያኔን በወሳንሳ ደግፈዉ ያቆሙት ምዕራባዉያን መንግስታትም ካዉቁ ቆይቷል። የዛሬ አራት አመት አካባቢ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ህዝብ ለሚያደርገዉ ሰላማዊ ትግል መሳሪያ ናቸዉ ወይም ይሆናሉ ብሎ ያመነባቸዉን የተቃዉሞ ሰልፍ የማድረግንና ሀሳብን በጽሁፍና በንግግር የመግለጽ መብትን የሚያግዱ ሁለት ፀረ ህዝብና ፀረ አገር ህጎች አርቅቆ ማጽደቁ የሚታወስ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለዲሞክራሲ ማበብና መለምለም ዋስትና ሊሆኑ የሚችሉ የሲቪክ ማህበራትን የሚያደራጁና የሚረዱ አለም አቀፍ ድርጅቶች ኢትዮጵያ ዉስጥ እንዳይንቀሳቀሱ እጅና እግራቸዉን ጠፍሮ የሚያስር ህግ አዉጥቷል። ይህ ሁሉ የህግ ጋጋታ የኢትዮጵያን ህዝብ ለመጥቀም ሳይሆን በህግ ሽፋን ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነጻነት የሚታገሉ ኃይሎችን ለማጥፋት ነዉ። እስክንድር ነጋ፤ አንዱ አለም አራጌ፤ ርዕዮት አለሙ፤ በቀለ ገርባና ዉብሸት ታዬ የእነዚህ ህጎች ሰለባዎች ናቸዉ።

ዛሬ ህዝብ እንደከዳቸዉና ቀኑ እንደጨለመበቸዉ የተረዱት የወያኔ መሪዎች በየመስሪያ ቤቱ፤ በትምህርት ቤቱና በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ዉስጥ ሽብርተኝነትንና አክራሪነትን አስመልክቶ ስልጠና ካልሰጠን እያሉ ቁጭ ብድግ እያሉ ነዉ። እዚህ ላይ አንድ አጅግ በጣም የሚያሳዝን ነገር ቢኖር ይህ የወያኔ ስልጠና በዕድሜ ያልተገደበና ህፃናትንም የሚያጠቃልል መሆኑ ነዉ።ከአዲስ አበባና ከክልል ከተሞች የሚደርሱን ዜናዎች እንደሚያመለክቱት የኢትዮጵያ ህዝብ የወያኔን ትርጉም የለሽ ስልጠና አልቀበልም ማለቱ ብቻ ሳይሆን መሰልጠን የሚያስፈልጋችሁ እናንተ ናችሁ እያለ የወያኔን ካድሬዎች እያሳፈረ ወደመጡበት እየመለሰ ነዉ። ዕድሜያቸዉ በአስራዎቹ የሚቆጠር አንድ ፍሬ ልጆች ወፋፍራሞቹን የወያኔ ባለስልጣኖች “ለምን እናንተ ብቻ የምታዉቁ እኛ የማናዉቅ ይመስላችኋል” እኛኮ መረጃ የምናገኘዉ ከኢቲቪ ብቻ አይደለም እያሉ ላለፉት ሃያ ሁለት ማን ይናገረናል ብለዉ ልባቸዉን ያሳበጡትን የወያኔ ባለስልጣኖች እንደ ተነፈሰ ፊኛ አኮማትረዋቸዋል።

ወያኔ እስካሁን ድረስ ስልጠናዉን በሰጠባቸዉ ቦታዎች ሽብርተኛ ናቸዉ እያለ እንደምሳሌ የሚጠቀመዉ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብትና ነፃነት መከበር በህይወታቸዉ የቆረጡትን ግንቦት ሰባቶችንና የኦሮሞና የኦጋዴን ህዝብ እራሱን በራሱ ማስተዳደር እንዲችል ከእራሱ ከወያኔ ጋር የተዋደቁትን ኦነግንና ኦብነግን ነዉ። በሌላ በኩል ደግሞ አክራሪ ናቸዉ እያለ በምሳሌነት የሚያቀርበዉ የማምለክ መብታችን ይከበር ወይም የሐይማኖት መሪዎቻችንን እኛዉ እንምረጥ ብለዉ ፍጹም ሰለማዊ ትግል የጀመሩትን የእስልምና እምነት ተከታይ ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ነዉ። በጭንቅላታቸዉ ሳይሆን በተሸከሙት ጠመንጃ ብቻ የሚያስቡት የወያኔ መሪዎች በፍጹም ሊገባቸዉ አልቻለም አንጂ ከሽብርተኞችና ከአክራሪዎች ጋር አትተበባሩ እያሉ ስልጠና የሚሰጡት የኦነግን፤ የድምጻችን ይሰማና የግንቦት ሰባትን አላማ አቅፈዉና ደግፈዉ ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር አብረዉ ለመታገል ለቆረጡ ወጣቶች፤ ተማሪዎችና ሰራተኞች ነዉ። ለዚህ ነዉ በሽብርተኝትና በአክራሪነት ላይ ስልጠና ለመስጠት በሄዱበት ቦታ ሁሉ ህዝቡ ችግራችን ሙሰኝነትና ዘረኝነት ወይም የመብትና የነጻነት መረገጥ ነዉ እንጂ አክራሪነትና ሽብርተኝት አይደለም እያለ የሚሞግታቸዉ።

ወያኔ እሱ እራሱ ሽብርተኛ በሆነበት አገር ዉስጥ ሰላማዊ ዜጎችን ሽብርተኛና አክራሪ እያለ ድፍን አገርን እንቅልፍ የሚነሳዉ ኢትዮጵያ በእርግጥም የሽብርተኞችና የአክራሪዎች አገር ሆና አይደለም፤ ደግሞም የሽብርተኝነትና የአክራሪነት አደጋ አራችንን ዉስጥ ኖሮ ቢሆን እንኳን እሱ እራሱ አሸባሪ የሆነው ወያኔ ክሽብርተኝነት ጋር አይጣላምና ይህ የምንመለከተዉ የወያኔ ሽርጉድ ሽብርተኝነትን ለመከላከል አይደለም። የወያኔ ብቸኛ አላማ በጉልበት የያዘዉን ስልጣን በጉልበት ዘለዓለማዊ ማድረግ ነዉ። የነጻነት፤ የፍትህ፤ የዲሞክራሲና የእኩልነት አርማ አንግበዉ የሚታገሉ ወገኖችን ሽብርተኞች ብሎ የፈረጀዉም በህግ ሽፋን እነዚህን የሰላም ኃይሎች ለመደምሰስ ነዉ። የወያኔ ዘረኞች ከ1997ቱ ምርጫ በኋላና ከዚያም በፊት በደኖ፤አሶሳ፤ አርባጉጉና ጋምቤላ ዉስጥ በወሰዱት ፀረ ህዝብ እርምጃ ዛሬም የኢትዮጵያን ህዝብ በጅምላ ከመግደል የማይመለሱ ጨካኞች መሆናቸዉን በተግባር ያስመሰከሩ አረመኔዎች ናቸዉ። ዛሬ ወያኔም ሆነ ኢህአዴግ በመካከላቸዉ በተፈጠረ የስልጣን ሽኩቻና ተቃዋሚ ኃይሎች በፈጠሩባቸዉ ከፍተኛ ግፊትና ጫና የተነሳ የተበታተኑበትና ግራ የተጋቡበት ግዜ ነዉ። ለዚህ ነዉ እንዳበደ ዉሻ ያገኙትን ሁሉ አክራሪና ሽብርተኛ እያሉ የሚለክፉትና በሰበብ ባስባቡ የሚቃወማቸዉን ሁሉ ለማጥፋት የሚሯሯጡት። የዛሬ 36 ዓመት ደርግ የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን ፀረ አብዮት ናችሁ እያለ አንድ ትዉልድ ጨፍጭፎ ጨርሷል። ዛሬም ወያኔ የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ጥያቄ ያነገቡ የህዝብ ልጆችን አክራሪና ሽብርተኛ ናችሁ እያለ ከደርግ የበለጠ ለመግደልና ለመጨፍጨፍ በዝግጅት ላይ ይገኛል።

ከላይ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ ወያኔ ህዝብን እንዳሰኘዉ ማሰር፤ መደብደብና መግደል እንዲችል የተለያዩ ህጎችን እርቅቆ አጽድቋል። ከሰሞኑ በግልጽ እንደምንመለከተዉ ደግሞ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ከዚህ በፊት ለፈጸሙትና ከአሁን በኋላም ለመፈጸም በሚያስቧቸዉ የዘር ማጥፋት ወንጀሎች የማይጠየቁበትን መንገድ ካሁኑ እያዘጋጁ ነዉ። ይህንን ለማድረግ ደግሞ እንደነሱ እጃቸዉ በህዝባቸዉ ደም የታጠበ የአፍሪካ አምባገነኖችን በማስተባበር ላይ ይገኛሉ። አንድ መረሳት የሌለበት ነገር ቢኖር በአንድ በኩል እንደ አባይ ፀሐዬ፤ ጌታቸዉ አሰፋና ሳሞራ የኑስን የመሳሰሉ ነብሰ ገዳዮች አኝዋክ ዉስጥ በፈፀሙት የዘር ማጥፋት ወንጀል አንድ ቀን መጠየቃቸዉ እንደማይቀር ያዉቃሉ። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን የለየላቸዉ ነብሰ ገዳዮች አለም አቀፉ ፍርድ ቤት በዘር ማጥፈት ወንጀል ቢከስሳቸዉ እንኳን ወንለኞቹ በአገር መሪነት ቦታ ላይ እስከተቀመጡ ድረስ እጃቸዉን ይዞ ለፍርድ የሚያቀርባቸዉ ኃይል አይኖርም። ይህንን ደግሞ እነ አባይ ፀሐዬ ከሱዳኑ አቻቸዉ ከአልበሺር ተምረዋልና በሚጋባ ይረዳሉ። ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያዉያን መከፈል ያለበትን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍለን እነሱንና ዘረኛ ስርዐታቸዉን እስካልደመሰስን ድረስ የወያኔ ዘረኞች እኛንም አገራችንንም እያደሙ የስልጣን ዘመናቸዉን ለማራዘም የማያደርጉት ነገር አይኖርም።

ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ባለፉት ሃያ ሁለት አመታት በኢትዮጵያ ህዝብና በአንድነቱ ላይ የፈጸሟቸዉ ወንጀሎች በአገር ዉስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ በህግ የሚያስጠይቁ ከባድ ወንጀሎች ናቸዉ። ለምሳሌ በአኝዋክ ህዝብ ላይ የፈፀሙት የዘር ማጥፋት ወንጀልና አዲስ አበባ ዉስጥ ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ የፈጸሙት የጅምላ ግዲያ አንድ ቀን አገር ዉስጥም በአለም አቀፍ ደረጃም የሚያስጠይቁ ወንጀሎች ናቸዉ። የወያኔ ኢህአዴግ ስርአት እስካልተወገደ ድረስ አገር ቤት ዉስጥ እነዚህን ዘረኞችና ወንጀለኞች ለፍርድ ማቅረብ አይቻልም። በአለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን ወያኔ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ እነ አባይ ፀሐዬን፤ ሰብሀት ነጋን፤ጌታቸዉ አሰፋንና ሳሞራ የኑስን የመሳሰሉ ቱባ ቱባ ወንጀለኞች ለፍርድ አሳልፎ የሚሰጥ ኃይል የለም። እንግዲህ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች አገር ዉስጥም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ላለመጠየቅ ያላቸዉ ብቸኛ አማራጭ ስልጣን አለመልቀቅ መሆኑን በሚገባ ያዉቃሉ ማለት ነዉ። ለዚህም ነዉ የኢትዮጵያን ህዝብ እያሰሩ፤ እየደበደቡና እየገደሉ ስልጣን ከእጃቸዉ አንዳይወጣ የሚታገሉት፤ ይህ ከሰሞኑ ሽብርተኛና አክራሪ እያሉ በየቦታዉ መስጠት የጀመሩት ስልጠናም የዚሁ የስልጣን ማቆያዉ ትግል ነዉ። ወያኔዎች ስልጣን ላለመልቀቅ የሚቻላቸዉን ሁሉ ቢያደርጉም እነሱም ሆኑ የገነቡት ዘረኛ ስርዐት አንድ ቀን ተንኮታኩቶ መዉደቁ እንደማይቀር ያዉቃሉ። የሚገርመዉ ወያኔዎች ለዚህም ዘዴ አላቸዉ፤ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የመለስ ራዕይ ብሎ ነገር የለም - ስብሀት ነጋ

ኢህአዴግ ዉስጥም ሆነ ህወሃት ዉስጥ የፓርቲ አባላቱ የጋራ ራዕይ እንጂ “የመለስ ራዕይ” የሚባል ነገር የለም ሲል የህወሃት መስራችና አባት የሆነዉ ስብሃት ነጋ ተናገረ። ስብሃት ነጋ ይህንን ብዙዎችን ግራ ያጋባ ንግግር የተናገረዉ በቅርቡ ሰሜን አሜሪካ መጥቶ በነበረበት ወቅት ከዘሀበሻ ጋዜጣ ጋር ባደረገዉ ቃለምልልስ ወቅት ነዉ። በደጋፊዎቹና በፓርቲ አባላቱ አካባቢ “አቦይ ስብሀት” በሚል ስም የሚታወቀዉ ሰብሀት ነጋ አፉ እንዳመጣለት የሚናገር ሰዉ መሆኑን ደጋግሞ ያሳየን ቢሆንም ይህ ከሰሞኑ ዋሺንግተን ዲሲ ዉስጥ ለሚገኝ የተቃዋሚዉ ጎራ ጋዜጠኛ ለሆነዉ ደረጀ ደስታ በሰጠዉ ቃለ ምልልስ ዉስጥ የተናገራቸዉ አንዳንድ ዉስጠ ወይራ ንግግሮች ግን ከዚህ ቀደም ካደረጋቸዉ ንግግሮች ሁሉ የተለዩና ሆን ብሎ ተዘጋጅቶ ያደረጋቸዉ ንግግሮች ስለ መሆናቸዉ ብዙዎች ይስማሙበታል።

በተለይ ስብሀት ነጋ እራሱ በፈጠረዉና ለረጂም ግዜ በመራዉ በህዝባዊ ወያነ ሀርነት ትግራይ(ህወሀት) ውስጥ የተካረረ አለመግባባት እንዳለ በሚነገርበት በአሁኑ ወቅት አንደኛዉን የህወሀት ቡድን እንደሚመራ የሚነገርለት ስብሀት ነጋ “የመለስ ራዕይ” የሚባል ነገር የለም ብሎ መናገሩ ከሟቹ የትግል ጓደኛዉ ባለቤት ከአዜብ መስፍን ጋር ያለዉን የተካረረ አለመግባባት በግልጽ ያሳያል። አዜብ መስፍንና ኃይለማሪያም ደሳለኝ የመለስ ዜናዊን ራዕይ ከግቡ እናደርሳለን ብለዉ ምለዉ በተነሱበት በአሁኑ ወቅት ሰብሀት ነጋ፤ እነ ኃይለማሪያም የሽብርተኞች ደጋፊ እያሉ ለሚጠሯቸዉ የዳያስፖራ ጋዜጠኞች የሰጠዉ ቃለመጠይቅና የቃለመጠይቁ ይዘት የሚያሳየዉ አንድ ትልቅ ቁም ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ ዉስጥ የህወሃት ዘመን እያበቃለት መሆኑንና ጠንከር አድርጎ የሚገፋዉ ኃይል ከተገኘ ወድቆ ሊከሰከስ እንደሚችል ነዉ።

መለስ የ ኢህአዴግን ራዕይ ለማስፈፀም ከፊት ሆኖ ብዙ ሥራ ሠራ እንጂ ራዕዩ የመለስ አይደለም። ራይዩ የድርጅቱ ነው” ያለዉ ስብሀት ነጋ በዚሁ ቃለምልልሱ ከሟች ጠቅላይ ሚኒስትር ባለቤት ከአዜብ መስፍን ጋር አለመግባባት ውስጥ ገብቶ እንደነበር በግልጽ ተናግሯል። ከዚህ በተጨማሪ የመለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ ስለተሾሙት 33 ጀነራሎች ምንም የሚያውቁ ነገር በማለት ብዙዎችን ያስገረመና ግራ ያጋባ ንግግር አድርጓል። የኃይለማሪያም ደሳለኝን አመራር በተመለከት የቀረበለትን ጥያቄ ሲመልስ ጥያቄ፡-በጋራ፣በኮሚቴ አገር እየመራን ነዉ ብሏል።

## የፌዴራሉ አቃቤ ህግ የቀድሞ የህወሀት አባላት መኖሪያ ቤት ዉስጥ የጦር መሳሪያ ክምችት ማግኘቱን ገለጸ

አዲስ አበባ ዉስጥ ከሚገኙ ዘጋቢዎቻችንና ከተለያዩ ምንጮች በሚደርሱን መረጃቸዎች መሰረት የወያኔዉ አቃቤ ህግ በቀድሞው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋ/ዳይሬክተር መላኩ ፋንታ መዝገብ በተከሰሱት ሁለት የህወሀት አባላት መኖሪያ ቤት ዉስጥ የአገሪቱ ህግ ከሚፈቅደዉ ዉጭ ብዛት ያላቸዉ የጦር መሳሪያዎች ተከማችተዉ ማግኘቱን መግለጹ ተሰማ። እንደ አቃቤ ህጉ አገላለጽ በቀድሞዉ የህወሀት አባልና የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ምክትል ዳይሬክተር በነበረዉ በአቶ ገብረዋህድ ወ/ጊዮርጊስ መኖሪያ ቤት ውስጥ 2 ታጣፊና ባለእግር ክላሾች፣ 4 ማካሮቭ ሽጉጦች፣ 2 ኮልት ሽጉጦች፣እና አንድ ስታር ሽጉጥ በድምሩ 9 የጦር መሳሪያዎች መገኘቱ የታወቀ ሲሆን በሌላው የህወሀት አባልና በ24ኛው ተከሳሽ በቀድሞው የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት አማካሪ በነበረዉ በአቶ ወልደስላሴ ሚካኤል ቤት ደግሞ 2 ባለሰደፍና ታጣፊ ጠመንጃዎች፣ አንድ ኡዚ ጠመንጃ፣ አንድ እስታር ሽጉጥ፣ አንድ የጭስ ቦንብና የተለያዩ ጥይቶችን ይዞ ማገኘቱ ተገልጿል። ወልደስላሴ /ሚካኤል የተባለዉ ግለሰብ ከቀድሞው ጠ/ሚ አቶ መለስ ዜናዊ ባለቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ጋር የቅርብ ግኑኝነት እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ይሄዉ ግለሰብ ከደህንነቱ ሹም ከጌታቸው አሰፋ ጋር ከፍተኛ ቅራኔ ዉስጥ የገባ ሰዉ ነዉ። እንደ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ግምት ወልደስላሴ ገ /ሚካኤል የታሰረዉ ወያኔዎች እንደሚሉት በሙስና ብቻ ሳይሆን ከጌታቸው አሰፋ ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ነዉ የሚል ከፍተኛ እምነት አለ።

የኢትዮጵያ ህግ አንድ ግለሰብ ከመንግስት በማስፈቀድ አንድ የነፍስ ወከፍ መሳሪያ እንዲይዝ የሚፈቅድ ቢሆንም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ምንም አይነት አመኔታ የሌለዉ ወያኔ ግን ከቤት ወደ ቤት እያዞረ ህዝቡን መሳሪያ ማስፈታቱ የሚታወስ ነዉ ። በሌላ በኩል ደግሞ በ1997 ምርጫ በኋላ ወያኔ የትግራይ ብሄረሰብ ለሆኑ ግለሰቦችና ለህወሀት አባላት እራሳችሁን ጠብቁበት ብሎ መሳሪያ በገፍ ማደሉ ይታወቃል። አሁን በቅርቡ የወያኔዉ አቃቤ ህግ በገብረዋህድና በወልደስላሴ መኖሪያ ቤት ዉስጥ አገኘሁ ያለዉ መሳሪያም ቢሆን ግለሰቦቹ የህወሀት አባል በነበሩበት ግዜ የተሰጣቸዉ መሳሪያ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለዉም። ሆኖም በእነዚህ ሁለት ግለሰቦች ቤት ዉስጥ የተገኘዉ መሳሪያ ብዛት የሚያሳየዉ ወያኔ ከትግራይ ተወላጆች ዉጭ ሌላ ማንም ሰዉ እጅ መሳሪያ እንዲገባ በፍጹም እንደማይፈልግና ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚታመኑትም እራሳቸዉን እንዲጠብቁ የሚፈቀድላቸዉ የትግራይ ተወላጆች ብቻ መሆናቸዉን ነዉ።ሌላዉ እጅግ የሚያሳዝነዉና የፌዴራሉ አቃቤ ህግ በመላኩ ፋንታ ላይ ከመሰረታቸዉ ክሶች አንዱ የሆነዉ ግለሰቡ የስራ ኃላፊነቱን በመጠቀም ለስራ ጉዳይ የመጣችን ሴት፤ ትዳሯን ፈትታና በትዳር ውስጥ ያፈራቻቸውን ሦስት ልጆች በትና አብራው እንድትሆን ማድረጉ ነዉ። ይህ በብዙ የወያኔና የኢህአዴግ ባለስልጣኖች ላይ የሚታየዉ የግልሙትና ችግር ወያኔና ስርዐቱ ምን ያህል እንደበሰበሱና ብዙዎቹ የወያኔ/ኢህአዴግ አባላት እንኳን ለኢትዮጵያ ለራሳቸዉና ለቤተሰቦቻቸዉም የማይበጁ ጋጠወጦች መሆናቸዉን ነዉ።

## የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ወያኔን ለመደምስ ዝግጁ ነኝ አለ

የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ዴምሂት ሊቀመንበር ታጋይ ሞላ አስገዶም ሰራዊታቸው ባለፉት አመታት ከወያኔ ሰራዊት ጋር በመግጠም በተለያዩ ወቅቶች በጠላት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን ለግንቦት 7 ንቅናቄ ሬድዮ በሰጡት ቃለምልልስ አስረዱ። ከተመሰረተ 12 አመታትን ያስቆጠረው የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር በ1993 ዓ.ም ቁጥራቸው አነስተኛ በሆኑና የወያኔ አገዛዝ ባንገፈገፋቸው ታጋዮች የተቋቋመ ሰራዊት ሲሆን በአሁኑ ወቅት በብዙ ሺህ በሚቆጠር የሰው ሃይል እንደተደራጀ ታጋይ ሞላ አብራርተዋል።ዴምሂት በወታደራዊ ስልጠና በአካል ብቃትና በፖለቲካ ትምህርት ብቁ የሆነ ስልጠና ያደረገ ሲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት የሆነውን የወያኔ ጉጅሌ አገዛዝ በማስወገድ ሕዝብን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ ለሚደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል በቁርጠኝነት እየተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል።የንቅናቄው ሊቀመንበር ታጋይ ሞላ እንደተናገሩት ዴምሂት በኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ላይ የማያወላውል የጸና እምነት ያለው ድርጅት መሆኑንና የኢትዮጵያን ብሔራዊ አንድነት ለማስከበር እንዲሁም ህዝብን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ ከሚታገሉ ድርጅቶችና ሐይሎች ጋር በጋራ ለመስራት እና መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

## የህወሀቱ ተካ አባዲ የብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ስራ አስኪያጅ ሆኖ ተሾመ

በንግስት ነገስታት ዘዉዲቱ ዘመነ መንግስት የተመሰረተዉንና አራት መንግስታትን ያገለገለዉን አንጋፋዉን የብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ላለፉት ሃያ አመታት የመሩት ወ/ሮ ሙሉወርቅ ገብረህይወት በቅርቡ በጡረታ ሲገለሉ በምትካቸዉ የህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ አባል የሆነዉ ተካ አባዲ መሾሙን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። ተካ አባዲ ለረጂም ግዜ የአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሰራ ሲሆን በመጥፎ ጸባዩና በአስተዳደር ብልሹነቱ በሰራተኞች አካባቢ የተጠላ ሰዉ መሆኑ ይነገርለታል። የተካ አባዲን መጥፎ ባህሪይና ለሰራተኞች ያለዉን ግድ የለሽነት የሚያዉቁት የብርሀንና ሰላም ሰራተኞች የዚህን ሰዉ ሹመት ሲሰሙ በድንጋጤ መዋጣቸው ተሰምቷል። የቀድሞዋ ስራ አስክያጅ ወ/ሮ ሙሉወርቅ ገብረህይወት የኢህአዴግ ደጋፊ ቢሆኑም፣ ከሰራተኛው ጋር ተግባብተው በመስራት የተመሰገኑ እንደነበሩ ብዙዎች የማተሚያዉ ቤት ሰራተኞች መስክረዉላቸዋል።

የግንቦት ሰባት ዘጋቢዎች ዉስጥ አዋቂ ምንጮችን ጠቅሰዉ በላኩልን መረጃ መሰረት የተካ አባዲ ሹመት ከችሎታና ከብቃት ጋር የተያያዘ ሳይሆን ወያኔ የአገሪቱን ትልቁን ማተሚያ ቤት በቅርብ ለመቆጣጠር ሆን ብሎ የሰጠዉ ሹመት ነዉ። የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ያቋቋመው የሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377 ስራ አስኪያጆችን የሚሾመው የስራ አመራር ቦርድ መሆኑንና ማስታወቂያ በጋዜጣ ወጥቶ አቅም ያለው ሰው ሁሉ ተወዳድሮ የሚገባበት አንደሆነ በግልጽ ያስቀመጠ ቢሆንም፣ ተካ አባዲ ግን ምንም ማስታወቂያ ሳይወጣ በወያኔ ቀጥታ ትእዛዝ እንዲሾም ተድርጓል። የስራ አመራር ቦርዱ ለልማት አጀንሲው በተደጋጋሚ ማስታወቂያ እንዲወጣ ደብዳቤ ቢልክም፣ የወያኔ ባለስልጣኖች ባደረጉት ተጽእኖ የተነሳ ማስታወቂያዉ ሳይወጣ ቀርቷል። ስር የሚገኘው ኤጀንሲ በቀጥታ አቶ ተካ እንዲሾሙ አድርጓል።

ተካ አባዲ በአዲስ አበባ የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ውስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወት ሰዉ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን ለዚህ በቅርቡ ለተሰጠዉ ሹመት ያበቃዉ የትግራይ ተወላጅነቱና ለወያኔ ያለዉ ታማኝነት ነዉ። ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ጋዜጦችና መጽሄቶች የሚታተሙበት ቦታ ስለሆነ ወያኔ ለማተሚያ ቤቱ የራሱን ሰዉ መሾሙ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

# ፕራይቬታይዜሺን ኤጀንሲ በወያኔ ጫና መማረሩን ይፋ አወጣ

በመንግስት ይዞታ ስር የሚገኙ የተለያዩ የማምረቻ፤ የማከፋፈያና የአገልግሎት ድርጅቶችን ለግል ባለንብረቶች የመሸጥና የመለወጥ ስልጣን ያለዉ ፕራይቬታይዜሺን ኤጀንሲ የወያኔ ባለስልጣኖች በፈጠሩበት ከፍተኛ ጫና የተነሳ የተሰጠዉን የስራ ተግባር ማከናዉን እንዳቀተዉ የኤጀንሲው የስራ ሃላፊ ለኢሳት ቴሌቪዥንና ሬድዮ ዘጋቢዎች መናገራቸዉ ተሰማ። ለሽያጭ የሚቀርቡ ድርጅቶችን ለመግዛት የሚመጡት ባለሃብቶችና የወያኔ ባለስልጣኖች በጥቅም የተሳሰሩ መሆናቸዉና ብዙዎቹ ባለስልጣኖች ባለሀብቶችም መሆናቸዉ በፕራይቤታይዜሺን ኤጄንሲ በኩል በሚሸጡ የመንግስትና የህዝብ ንብረት አገሪቱ ምንም እንደማትጠቀም የኤጄንሲዉ ስራ አስኪያጅ ተናግረዋል። ካሁን በፊትም፤ የአዋሺ አግሮ ኢንዱስትሪ ቲብላ እርሻ ወደ ግል የተዛወረበት መንገድ ግልጽነት የጎደለው ስምምነት ነበር፡፡

በሰሜን ኦሞ እርሻ ልማት ውስጥ የሚገኘው ሞራቴ እርሻ ልማት ድርጅት መሸጥ ከሚገባቸዉ ዋጋ በታች ከተሸጡት ድርጅት መካከል ቀዳሚው እንደነበር የገለጹት እኙሁ ባለስልጣን ይህ የኮሪያ ባለሃብቶች ንብረት የነበረዉ የእርሻ ልማት ድርጅት ወደ ግለሰቦች ሲዛወር ፍጹም ከህግ ከአሰራር ቁጥጥር ውጭ በሆነ መንገድ በስጦታ እንደ ተላለፈ ነዉ የማየዉ እንጂ ተሸጠ ብዬ አላምንም ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛዎቹ ድርጅቶች በሽያጭ ወደ ግላ ባለኃብቶች እጅ ሲገቡ የብዙ አመት ልምድ ያላቸዉ ሰራተኞች እየተባረሩ በምትካቸዉ የባለንብረቶቹ ዘመዶችና የገዢዉ ፓርቲ ደጋፊዎች እንደሚቀጠሩ ታዉቋል። እንዲህ አይነቱ አሰራር በአንድ በኩል በምርታማነትና በአገሪቱ ዕድገት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ ሲሆን ረጂም ግዜ ከሰሩበት ቦታ የሚባረሩት ሰራተኞችና ቤተሰቦቻቸዉ ከፍተኛ ችግር ዉስጥ የወድቃሉ።

ከጥቂት አመታት በፊት ፕራይቬታይዜሺን ኤጄንሲ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ግብርና ሜካናይዜሽንና ግዮን ሆቴል ለግል ባለኃብቶች እንዲሸጡ ጨረታ ካወጣ በኋላ ትንሽ ቆይቶ ከእነዚህ ኩባንያዎች ጋር ሌሎች ሦስት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ማለትም የአርሲ ባሌ እርሻ ልማት ድርጅቶች፣ የኮንስትራክሽን ሥራዎችና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ኢንስቲትዩት ለሽያጭ እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ገንዘብ ሚኒስቴር ጨረታዉ አየር ላይ እንዳለ ሦስቱ ድርጅቶች እንዳይሸጡ በመወሰኑ ከጨረታ ሒደቱ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ ከዚያም የአርሲና ባሌ እርሻ ልማት ድርጅቶችን ለኦሮሚያ ምርጥ ዘር ድርጅት፣ እንዲሁም የኮንስትራክሽንና ቡና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ኢንስቲትዩትን ለብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን እንዲሰጡ ተደርጓል፤ እነዚህ ሁለት ተቋሞች ደግሞ የወያኔ ተቀጽላዎች እንደሆኑ ሁሉም የሚያወቀዉ ሀቅ ነዉ።

የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ተመስርቶ ስራዉን ሲጀምር 287 ድርጅቶች በቁጥጥሩ ስር የነበሩ ሲሆን እስከ 2004 ዓ.ም. ድረስ 236 ድርጅቶችን ለግል ባለኃብቶች ሸጦ በአሁኑ ወቅት እጁ ላይ የሚገኙት 51 የልማት ድርጅቶች ናቸው፡፡ከእነዚህ ውስጥ ሃያዎቹን በ2005 ዓ.ም. ወደ ግሉ ዘርፍ ለማዛወር እቅድ አዉጥቶ ነበር። ኤጀንሲው የመንግሥትና የህዝብ ድርጅቶችን በሽያጭ ወደ ግሉ ዘርፍ ማስተላለፍ በጀመረበት በ1987 ዓ.ም. አምስት ኢንተርፕራይዞችን ብቻ ነበር ወደ ግሉ ዘርፍ ያዛወረው፡፡ በቀጣዩ ዓመት ግን እስከዛሬ ድረስ ድረስ ባልታየ መልኩ 127 የመንግሥትና የህዝብ ድርጅቶችን ለግል ባለኃብቶች ሸጧል፤ ሆኖም እነዚህ የግል ባለኃብቶች የሚባሉት የህወሀት ሰዎችና እነሱ የሚቆጣጠሯቸዉ "ኤፎርትን" የመሳሰሉ ድርጅቶች በመሆናቸዉ ሽያጩ በእርግጥም ሽያጭ ሳይሆን በስጦታ መልክ የተካሄደ ሽያጭ ስለሆነ በእነዚህ ድርጅቶች ሽያጭ ግብር ከፋዩ የኢትዮጵያ ህዝብ የራሱ ንብረት ሲሸጥ ጭራሽ እንደ ባዳ ተቆጥሮ ከስራ እየተባረረ እሱና በተሰቦቹ ችግር ዉስጥ ወደቁ እንጂ ምንም አይነት ጥቅም አላገኘም።

## የህወሀቱ ተካ አባዲ የብርሀንና . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የሚያመለክተዉ ይህ ጸረ ህዝብ ድርጅት እሱ ከሚፈልገዉ ዉጭ ምንም ነገር እንዳይታተለም ለማድረግ ያለዉን ፍላጎት መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል። ባለፉት አንድና ሁለት አመታት ፍትህ፣ ፍኖተ ነጻነትና ሌሎች መንግስትን ይቃወማሉ የሚባሉ ጋዜጦች በብርሀንና ሰላም መሪዎች እንዳይታተሙ መደረጉ የሚታወቅ ሲሆን አዲሱ ስራ አስኪያጅ ተካ አባዲም ይህንኑ የመንግስት አፈና ፖሊሲ ያስቀጥላል ተብሎ ከፍተኛ እምነት ተጥሎበታል።

## ፋሽስት ወያኔ አሁንም በማስፈራራት . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ሳይቀር በሀገሪቱ ስለሌለው ሽብር ለማሰልጠን መሞከሩ እና ሌሎችም የሚያሳዩት ፋሽስት ወያኔ ከመቼውም በላይ በፍርሃት እየተንዘፈዘፈ መሆኑን አመላካች ነው" ብለዋል።

ፋሽስት ወያኔ ቀጣዩን የይስሙላ ምርጫ እንደለመደው 99.6 በመቶ አሸነፍኩ ለማለት አሁን የሕዝብን ልብ ትርታ እየገዙ ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በዚህም በዚያ ብሎ በማስወገድና ብቻውን ለመወዳደር ካሁኑ የጥቃት እርምጃ ለመጀመር ዝግጅት ላይ ነው የሚሉ ጥቂቶች አይደለም። ለዚህ ደግሞ የሰሞኑ የሃይለማሪያም ከሽብር ጋር የተያያዘ ድንፋታ ከበቂ በላይ አስረጂ እንደሆነ

## ኦብነግ በወያኔን ባለስልጣናት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የኦጋዴን ነጻነት ግንባር ኦጋዴን ዉስጥ በወያኔ ባለስልጣኖችና በዉጭና በአገር ዉስጥ ባለኃብቶች ላይ ጥቃት ሲፈጽም ይህ የመጀመሪያ ግዜዉ እንዳልሆነና ከዚህ ቀደም በፈጸመቻዉ ጥቃቶች በወያኔ ላይ ከፍተኛ የህይወት፤ የንብረትና የድፕሎማሲ ጉዳት ማድረሱ የሚታወስ ነዉ። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ኦጋዴን የሰላም ወረዳ ነዉ እያለ የተለያዩ ባለኃብቶችን በክልሉ የፔትሮሊየምና የተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋ ላይ እንዳሳተፉ ተደጋጋሚ ጥሪ ቢያደርጉም ኦብነግ በማሌዥያዉ ፔትሮናስ ኩባኒያ ላይ ጥቃት ፈጽሞ ከፍተኛ ጉዳት ካደረሰና ፔትሮናስ ጓዙን ጠቅልሎ ከኦጋዴን ከወጣ በኋላ ክልሉን የሚደፍር የዉጭ ባለኃብት አልተገኘም። ኦጋዴን የወያኔ መሪዎች የሰዉ ማጥፋት ወንጀል ከፈጸሙባቸዉ የኢትዮጵያ ክልሎች አንዱ ሲሆን በቅርቡ የወያኔ አገዛዝ በኦጋዴን ክልል የሚፈጽመዉን የዘር ማጥፋት ወንጀል የሚያሳይ ዘጋቢ ፊልም ሲዊድን ዉስጥ በቴሌቪዥን ከቀረበ በኋላ ፊልሙን የተመለከቱ ስዊድናዉያንና ሌሎችም አለም አቀፍ ጠበቆች ጉዳዩን ወደ አለማቀፉ ፍርድ ቤት ለመውሰድ እስካሁን ድረስ ያልታየ ትልቅ ንቅስቃሴ መጀመራቸዉ የሚታወስ ነዉ። አብነግ እንዲህ አይነቱን ወንጀል ለመከላከልና የኦጋዴን ክልል እራሱን ማስተዳደር አንዲችል የሚታገል በ1976 ዓም የተቋቋም ድርጅት ነዉ።

## ወያኔና አላርፍ ያለች ጣት . . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ባለፉት ሁለትና ሦስት ሳምንታት በግልጽ እንዳየነዉ ወያኔዎች የእነሱን ብጤ ነብሰ ገዳይ የአፍሪካ መሪዎች አስተባብረዉ አፍሪካን ከአለም አቀፉ ፍርድ ቤት ራዳር ዉጭ ለማድረግ ቁጭ ብድግ እያሉ ነዉ።

ይህ ሁሉ አገር ዉስጥና በአለም አቀፍ ደረጃ የሚደረግ ሩጫና ግርግር የሚያሳየዉ ወያኔ የኢትዮጵያን ህዝብ እየረገጠ ለመግዛት የሚያደርገዉ ትግል በአገር ቤት ዉስጥ ብቻ የተወሰነ አለመሆኑን ነዉ። ወያኔ የሚታገለን አገር ቤት ዉስጥ በጠመንጃዉ፤ በአህጉር ደረጃ እሱን ከመሰሉ አምባገነን የአፍሪካ መሪዎች ጋር የጋራ ህብረት በመፍጠር፤ በአለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ከዕርዳታ ሰጪ አገሮችና ድርጅቶች ጋር እጅና ጓንት በመሆን ነዉ። እንግዲህ ወያኔ አንዲዚህ በየመድረኩ የሚዋጋን ከሆነ እኛ ወያኔን ለማስወገድ የምንታገል ወገኖች የምናደርገዉ ትግል እነዚህን ዘርፈ ብዙ የወያኔ የትግል መድረኮች የሚመጥን ብቻ ሳይሆን የወያኔን ጥረቶች ሁሉ ጥሶ የሚሄድ የትግል ስትራቴጂ ያስፈልገናል ማለት ነዉ። ወያኔ ሽብርተኛና አክራሪ እያለ ህዝብን ሲያስፈራራ የህዝብ ተስፋና ተገን መሆን፤ ወያኔ በፈፀማቸዉ የዘር ማጥፋት ወንጀሎች ላለመጠየቅ ሲሞክር ሙከራዉን ማክሸፍ፤ወያኔ የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም ሲፍጨረጨር ደግሞ የስልጣን ዘመኑ እንዲያጥር ማድረግ የተቃዋሚዉ ጎራ የቀን ከቀን ስራዎች ሊሆኑ ይገባል።

ዛሬ በግልጽ አንደምንመለከተዉ ወያኔን ለማስወገድ ከመተባበር ዉጭ ሌላ አማራጭ የሌላቸዉ ተቃዋሚ ኃይሎች እርስ በርስ ሲባሉና ሲካሰሱ ወያኔ ግን የተቃዋሚ ጎራዉን ጨምሮ ይጠቅሙኛል ብሎ ከሚያስባቸዉ ኃይሎች ሁሉ ጋር ትብብር እየፈጠረ ነዉ። ወያኔንና ዘረኛ ስርዐቱን ከአገራችን ማጥፋት ካለብን ወያኔ ከዉስጥም ከዉጭም ተወጥሮ መግቢያና መዉጫያዉ የጠፋዉ ዛሬ ነዉና ይህንን እርስ በርስ በመካሰስ የምናጠፈዉን ግዜ፤ጉልበትና እዉቀት አቅጣጫዉን ለዉጠን በወያኔ ላይ አብረን እንዝመት።